EthioLion
የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ነሐሴ 2 2000 ዓ.ም.

# የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን መሬት ለሳዑዲ አረቢያ አሳልፎ ሊሰጥ ተነሳ

አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በቅርቡ አረብ ኒውስ ለተባለ የሳዑዲ አረብያ ጋዜጣ በሰጠው መግለጫ "ብዙ መቶ ሺ ሄክታር ለም መሬት" ለሳዑዲዎች ሊሰጥ ዝግጁ መሆኑን ገልጿል፡፡ የሳዑዲ ሚኒስቴሮችና ከበርቴዎች በቅርቡ ለዚሁ ጉዳይ አዲስ አበባ ተገኝተው እንደነበር የተገለፀ ሲሆን በኢትዮጵያ መሬት ላይ ሳዑዲዎች እህል አምርተው የዜጎቻቸውን የምግብ አቅርቦት ለማረጋገጥ ይፈልጋሉ ተብሏል፡፡

ኢትዮጵያውያኖች ለረሀብ ተዳርገው፤ የኑሮ ውድነት ሕዝብን ለባሰ መከራ አጋልጦ ባለበት በአሁኑ ጊዜ የወያኔ ፀረ ኢትዮጵያ አገዛዝ የሀገሪቷን ለምና ስንዴ/እህል አምራች መሬት ለባዕድ ሊሰጥ/ሊሸጥ መነሳቱ ይህ ቡድን ምንኛ ፀረ ሕዝብ መሆኑን የሚያጋልጥ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተዘገበው የወያኔ ቡድን ለጅቡቲው አምባገነን ኦማር ገለህና ባለቤታቸው የእርሻ መሬት ሳይቀር የለገሰ ከመሆኑ ሌላ ከቋራ እስከ ጋምቤላ ድረስ ደግሞ መሬታችንን ለሱዳን ማስረከቡ ተጋልጧል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም በቅርብና ሩቅ ባዕድ ሀገሮች ለአደጋ ሲጋለጥ የቆየ መሆኑ እየታወቀ በሀገራችን ኤኮኖሚ ላይ የሳዑዲ አረብያ ይዞታ/ቁጥጥር እንዲስፋፋ በወያኔ መደረጉ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚጎዳ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እስካሁንም ሳዑዲ አረብያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ላይ ጫናዋ ከበድ ያለ መሆኑ የታየ ጉዳይ ነው፡፡ ለሱዳን የተሰጠው መሬት ማንም የማይኖርበት ምድረ በዳ የቆላ መሬት ነው በሚል አጓጉል ምክንያት/ማጠየቂያ ቀርቦ እንደነበረው ዛሬም ለሳዑዲ ሊሰጥ የታሰበው ለም መሬት ማንም ያላረሰው ነው የሚል ሰበብ ከወዲሁ እየተሰጠበት ነው፡፡ ሳዑዲዎች አርሰው ያመረቱትን ወደ ሀገራቸው ሊወስዱ ማሰባቸውን የደበቁት ሀቅ አይደለም፡፡

ሌሎች ዜጎች የኢትዮጵያን ለም መሬት አርሰው እህልና ምግብ እንዳያጡ ሲደረግ ኢትዮጵያውያን ግን በራሳቸው የተጫነው አገዛዝ ሀገራቸውን እየሸጠ ለረሀብ ሲዳርጋቸው ዓለም መታዘብ ግድ ሆኖበታል፡፡ ማወቅ የሚኖርብን ግን ባዕዳኖች ወያኔ ለነሱ የሚጠቅም ሥራ እስከሰራ ድረስ ስለ ጠባዩም ሆነ ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር የሚጨነቁበት አይደለም፡፡ ወያኔ ከባዕዳኖች ጋር የሚፈራረማቸው ስምምነቶች ሕዝብ የመረጠው ዴሞክራሲያዊ መንግስት ሀገራችን ስታገኝ "ሕጋዊነት" ይኖራቸዋል ብሎ መደምደም እንኳ ቢያስቸግር ቢያንስ

ጥቅማችንን ወደሚያስጠብቅ ለመቀየር እራሱን የቻለ ውጣ ውረድን የሚጠይቅ ሁኔታ ውስጥ ሀገራችንን እንደሚከታት ከወዲሁ ማጤኑ ተገቢ ነው::

ነጋ ጠባ የወያኔ አገዛዝ ግፍና ወንጀል እየጨመረና እየባሰ በመሄድ ላይ መሆኑ ግልፅ ሲሆን የዚህን አገዛዝ ዕድሜ በቆራጥ ትግል ካላሳጠርነው ሀገሪቷን ይህን መሰል ውስብስብና አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እየከተታት እንደሚቀጥል ለማንም ስውር አይደለም:: ከፍሎና ሸንሽኖ/ሸጠ ህልውናዋን አጠያያቂ ማድረጉ አይቀሬ ነው:: የኢትዮጵያ መሬትና ኤኮኖሚም በታሪካዊ የሀገሪቷ ተቀናቃኞችና ጠላቶች እጅ መግባቱም ለህልውናዋ ከባድ ጥቃት መሆኑ ሊሸፈን የሚችል አይደለም:: ይህ በወያኔ ቡድን የሚመራ መንግስት ተብዬ ምን ያህል ከሀገርና ከሕዝብ ጥቅም አንፃር አስፈሪ እንደሆነ ይህን በመሰል ግብሩ እያደር እያስመሰከረ ነው::

ከህዲውን የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቆራጥ ትግል እናሰወግድ!!

EthioLion.Com

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France